| English | Amharic |
| --- | --- |
| If you’re passionate about it, if you have something to say about it – say it. Use your voice. Your voice does matter. And you matter. | ስለ ጉዳዩ የጠለቀ ስሜት ካለዎት፣ ስለ ጉዳዩ መናገር የሚፈልጉት ነገር ካለ - ይናገሩ። ድምጽዎን ይጠቀሙ። ድምጽዎ ዋጋ አለው። እርስዎም ዋጋ አለዎት። |
| POLICY COUNCIL | የፖሊሲ ሸንጎ (POLICY COUNCIL) |
| Policy Council started as something that I went to because somebody said I’d be good at it and I found that everyone that comes to Policy Council is on a whole different level. Some people come because they need that social aspect. Some people come because they know and they can make a difference and they will make a difference and some people come because they want to help or give back something because of all the benefits that we get as parents. | የ Policy Council የተጀመረው አንድ ግዜ አንድ ሰው በዚህ ጉዳይ ጥሩ ማድረግ እንደምችል ነግሮኝ በመሄዴ ነበር፣ እናም ወደ Policy Council የሚመጡ ሰዎች ሁሉ በተለያየ ደረጃ ላይ ያሉ መሆናቸውን አግኝቼዋለሁ። አንዳንድ ሰዎች ማህበራዊ ገጽታውን ፈልገው ይመጣሉ። አንዳንድ ሰዎች ደግሞ ለውጦችን ማድረግ እንደሚችሉ ስለሚያውቁ ይመጣሉ፣ ከመጡም በኋላ ለውጦችን ያደርጋሉ፤ አንዳንድ ሰዎች ደግሞ መርዳት ስለፈለጉ ወይም ወላጆች እንደመሆናችን መጠን ለምናገኛቸው ጥቅሞች ሁሉ ውለታ ለመመለስ ይመጣሉ። |
| The cool thing about it is we have the choices and we help make the decisions. | የዚህ ጉዳይ ጥሩነቱ፣ ምርጫዎች አሉን እናም ውሳኔዎችን ለማድረግ እርዳለን። |
| (Maria speaking Spanish) | (ማሪያ የምትናገረው ስፓኒሽ ነው) |
| Every center is given the opportunity to have a parent representative. | እያንዳንዱ ማዕከል የወላጅ ተወካይ እንዲኖረው ዕድል ይሰጠዋል። |
| (Maria speaking Spanish) | (ማሪያ የምትናገረው ስፓኒሽ ነው) |
| And these parents have been part of the decisions that are made here. | እናም እነዚህ ወላጆች እዚህ የሚደረጉ ውሳኔዎች ላይ ተካፋይ ነበሩ። |
| You’re basically joining a group of parents to understand what, in depth, what your children are going through. You take that information and you learn and you work with others throughout your community, your friends, and your family to education them on what you’re learning and how you’re growing. | በመሠረቱ የወላጆች ቡድን አባል የምትሆኑት፣ ልጆችዎ በምን፣ በምን ያህል ጥልቀት፣ ምን ሁኔታ ላይ እያለፉ እንደሆነ ለመረዳት ነው። መረጃውን ወስደው ትምህርት ይቀስማሉ፣ እናም በመላው ማህበረሰብ ውስጥ ከሚገኙ ሌሎች ሰዎች፣ ጓደኞችዎ፣ እና ቤተሰብዎ ጋር አብረው ሆነው እርሶ እንዴት እየተማሩና እንዴት እድገት እያሳዩ እንደሆነ ያስተምሯቸዋል። |
| At a Policy Council meeting what happens is we meet for approximately four hours once a month and the parents come together. There’s parents and past parents. There’s staff that attend the meeting and various other people that are involved in Early Learning, Head Start, and ECEAP. | በ Policy Council ስብሰባ ላይ የሚደረገው፣ በየወሩ በግምት ለአራት ሰዓታት እንሰበሰባለን፣ እንዲሁም ወላጆቹ ይሰበሰባሉ። ወላጆች አሉ እንዲሁም ደግሞ ከዚህ በፊት የነበሩ ወላጆችም ይኖራሉ። በስብሰባው ላይ የሚገኙ የሥራ ባልደረቦችና በ Early Learning፣ Head Start፣ እንዲሁም ECEAP ላይ የሚሳተፉ ሌሎች የተለያዩ ሰዎችም ይኖራሉ። |
| Being there at the meeting, getting the information, and giving your opinion, or at least being a part of the group when we have the meetings and attending the meetings are very crucial. | በስብሰባው ላይ መገኘት፣ መረጃውን ማግኘትና ሃሳብዎን መስጠት፣ ወይም በስብሰባ ወቅት ቢያንስ የቡድኑ አባል መሆንና ስብሰባው ላይ መሳተፍ በጣም አስፈላጊ ነገሮች ናቸው። |
| We’re given a list of all the things that we’re going to work on for that day. So then, in some groups, we vote on things. We vote on policies. We can separate into subgroups when we have a bigger task to do and then we trust each of the parents as to their decision on whatever policy change we need to make. | በዚያን ቀን ላይ ለምናደርጋቸው ነገሮች ዝርዝር ተሰጥቶናል። ስለዚህም፣ በአንዳንድ ቡድኖች ውስጥ፣ በነገሮች ላይ ድምጻችንን እንሰጣለን። በፖሊሲዎች ላይ ድምጻችንን እንሰጣለን። ተለቅ ያሉ ተግባሮችን ማድረግ ካለብን፣ በንዑስ ቡድኖች እንከፋፈልና፣ መለወጥ በሚገባቸው የፖሊሲ ለውጦች ላይ ተገቢውን ውሳኔዎችን እንዲያስተላልፉ በእያንዳንዱ ወላጅ ላይ እምነታችንን እንጥላለን። |
| Each meeting we have some time that we have to speak about business. Part of the requirements and the guidelines for the grants from the federal government and the state government that we have to do. Me speaking like I know all this stuff, | በምናደርገው እያንዳንዱ ስብሰባ ላይ፣ ስለ ቢዝነስ መነጋገር ይኖርብናል። ይህም ማድረግ ያለብን የፌደራል መንግስትና የስቴት መንግስት የገንዘብ እርዳታ ግዴታዎችና መመሪያዎች ክፊሉ ነው። እኔ ይህንን ሁሉ እንደሚያውቅ ሰው ሆኜ አሁን ስናገር፣ በ Policy Council ውስጥ ለመሳተፍና የምናገረውን |

| | |
|---|---|
| it took me a few years to get involved in being with Policy Council to be able to speak and have some intelligence in what I'm talking about. | አስመልክቶ የተወሰነ እውቀት ለማግኘት ጥቂት ዓመታት ወስዶብኛል። |
| (Maria speaking Spanish) | (ማሪያ የምትናገረው ስፓኒሽ ነው) |
| It's very important because when you become part of this program, Policy Council… | ይህ በጣም አስፈላጊ ነው፣ ምክንያቱም የዚህ ፕሮግራም አካል ሲሆኑ፣ የ Policy Council… |
| (Maria speaking Spanish) | (ማሪያ የምትናገረው ስፓኒሽ ነው) |
| As parents, we find out the importance of our voice. | ወላጆች እንደ መሆናችን መጠን፣ የድምጻችን ዋጋ ምን ያህል እንደሆነ ማወቅ እንችላለን። |
| (Maria speaking Spanish) | (ማሪያ የምትናገረው ስፓኒሽ ነው) |
| We are part of the decisions that are made for this program. | ለዚህ ፕሮግራም የሚደረጉት ውሳኔዎች አካል ነን። |
| (Maria speaking Spanish) | (ማሪያ የምትናገረው ስፓኒሽ ነው) |
| This is what is called shared governance. | ይህ የጋርዮሽ አስተዳደር ይባላል። |
| The council directors have been incredible mentors and coaches for me. I've learned an incredible amount of communication skills, techniques, confidence with public speaking. | የሸንጎው ዳይሬክተሮች ለኔ የላቁ አርአያዎችና አሰልጣኞች ሆነው አግኝቻቸዋለሁኝ። በጣም የላቀ ሃሳብ የመለዋወጫ ልምዶችን፣ ቴክኒኮችን፣ በህዝብ ፊት ቆሜ የመናገር ድፍረትን ተምሬያለሁ። |
| There's a lot of things that I just didn't know and the education part of it was huge. Absolutely huge for me as a person and then for everyone that I work with. It's helped me – it's kind of hard to really explain it because there's so many different ways that it's helped you. A lot of the programs that we do, a lot of the things that we work with are… they may seem broad, but when you are able to expose people to different areas of the world, different areas of their community, different areas that they weren't really aware of before, and you start to crack open the window, and when they know there's a window, then it's pretty amazing. | እኔ የማላውቃቸው በጣም ብዙ ነገሮች ነበሩ፣ በተለይም የትምህርት ክፍሉ በጣም ሰፊ ነበር። እንደ አንድ ግለሰብ ለእኔ በጣም ሰፊ ሲሆን፣ ከኔ ጋራ ለሚሰሩትም ሰዎች ሁሉ እንደዚያ ነው። ለኔ በጣም ረድቶኛል - መግለጹ ትንሽ ሊያስቸግር ይችላል፣ ምክንያቱም የረዳበት የተለያዩ ብዙ መንገዶች ሊኖሩ ይችላሉ። እኛ የምናደርጋቸው ብዙዎቹ ፕሮግራሞች፣ እኛ የምንጠቀምባቸው ነገሮች… በጣም ሰፊ ይመስሉ ይሆናል፣ ግን ሰዎችን ለተለያዩ የዓለም ክፍሎች፣ ለተለያዩ የማህበረሰባችን ክፍሎች፣ ከዚህ በፊት ላልተገነዘቧቸው የተለያዩ አካባቢዎች ካስተዋወቅሃቸውና፣ መስኮቱን ትንንሽ ከፈት ማድረግ ከጀመርክላቸውና፣ መስኮት መኖሩን ሲገነዘቡ፣ ከዚያ በጣም አስገራሚ ይሆናል። |
| I feel it has given me the skills, it has given me the capacity, it has given me the qualifications for a good leader through the trainings we get through Policy Council. It has given me the understanding of diverse communities because we do a lot of race and equity trainings, too. It has given me skills in policy. We get chances to review policies, which I feel is something very good a parent can have. | እኔ እንደሚመስለኝ፣ በ Policy Council በኩል የምናገኛቸው ስልጠናዎች፣ ልምዶችን፣ አቅምን፣ እንዲሁም ለጥሩ መሪነት ብቁነትን አበርክቶልኛል። ዘርንና ተገቢነትን አስመልክቶ ስልጠናዎችን ስለምናደርግ፣ ስለ ተለያዩ ማህበረሰቦች ያለኝን ግንዛቤ አዳብሮታል። ፖሊሲን አስመልክቶ ልምዶችን እንድቀስም አድርጎኛል። ፖሊሲዎችን ለመገምገም ዕድል እናገኛለን፣ ይህም አንድ ወላጅ ሊኖረው የሚችል በጣም ጥሩ ነገር ነው ብዬ አስባለሁ። |
| Sitting at Policy Council I would hold my head down when they started looking around for someone to ask a question or to answer a question because I didn't want to speak. Where now, it's hard to make me be quiet. | መናገር ስለማልፈልግ፣ በ Policy Council ውስጥ፣ አንድ ጥያቄ የሚጠይቅ ሰው ወይም ለጥያቄ መልስ የሚሰጥ ሰው እንዳለ ለማየት ዞር ዞር ሲሉ፣ አንገቴን እደፋ ነበር። አሁን ግን፣ እኔን ዝም ለማሰኘት በጣም አስቸጋሪው ይሆናል። |
| Policy Council is important to me because it gives the parent of the children a voice in what is being done for the kids, for Early Learning. | የ Policy Council ለኔ በጣም አስፈላጊ ነው፣ ለዚህም ምክንያቱ፣ ለልጆቹ ወላጅ፣ በ Early Learning ውስጥ፣ በሚደረጉ ነገሮች ላይ፣ ድምጻቸው እንዲሰማ ያደርጋል። |
| Before I got involved in Policy Council, I wasn't aware of how much my children were learning or what they were doing at school, or even had a clue because I work a lot and I wasn't really | በ Policy Council ውስጥ መሳተፍ ከመጀመሬ በፊት፣ ልጆቼ ምን ያህል ይማሩ እንደነበር ወይም እትምህርት ቤት ውስጥ ምን ያደርጉ እንደነበር አላውቅም ነበር፣ ወይም ምንም ፍንጭ እንኳ አልነበረኝም፣ ምክንያቱም በጣም ብዙ እሰራ ስለነበር በእርግጥ |

| | |
|---|---|
| involved. So in this aspect it’s helped me gain my awareness. Understanding what they’re going through as children in these critical times and age, their emotions, what they’re learning, how they’re learning, and who they’re going to grow up to be. | ተሳታፊ አልነበርኩም። ስለዚህ በዚህ መስኩ፣ ግንዛቤ እንዳገኝ ረድቶኛል። በዚህ በጣም ወሳኝ በሆነ የልጅነት ግዜና ዕድሜ ውስጥ በምን ሁኔታ ላይ እያለፉ እንደሆኑ፣ ስሜታቸውን፣ ምን እየተማሩ እንደሆኑ፣ በምን መልክ እየተማሩ እንደሆኑና ማንን መስለው እንደሚያድጉ መረዳቱ። |
| To be on Policy Council and have a say in how my kids are being taught and what’s going on in their classrooms and actually be able to come directly and talk to someone face to face. Not send in a letter, not call a one-eight hundred number and leave a voice mail. They have Policy Council for parents to come in here and actually relay messages face to face and actually look someone in their eyes. You get quick responses that way and it’s huge, so you don’t have to wait too long for changes. Policy Council allows for parents to come in and say what they need to say and see changes really quickly, so it helps. | በ Policy Council ውስጥ መሆንና ልጆቼ እንዴት እንደሚማሩና በትምህርት ክፍላቸው ውስጥ ምን እየተካሄደ እንደሆነ ሃሳብ ማቅረቡ፣ በእርግጥ በቀጥታ መጥቶ ከአንድ ሰው ጋራ ፊት ለፊት መናጋገር መቻሉ። ደብዳቤ በመላክ ሳይሆን፣ የአንድ-ስምንት መቶ ስልክ ቁጥር ደውሎ መልእክት መተው ሳይሆን። ወላጆች እዚህ መጥተው ፊት ለፊት ተገናኝተው መልእክታቸውን እንዲያስተላልፉና በእርግጥ አንድን ሰው ፊት ለፊት ማየት የሚችሉበት Policy Council አዘጋጅተዋል። በዚህ መልኩ መልስ ባፋጣኝ ያገኛሉ፣ ይህም በጣም ትልቅ ነገር ነው፣ እናም ለውጦችን ለማየት በጣም ብዙ መጠበቅ አይኖርብዎትም። Policy Council ፣ ወላጆች መጥተው መናገር የሚፈልጉትን ነገር እንዲናገሩና ለውጦችንም በቶሎ እንዲያዩ ያስችላቸዋል፣ እናም ጠቃሚ ነው። |
| Hopefully everybody will join Policy Council. It’s really important, reason being that you’ll learn a lot, you’ll grow, and they’re there to make you a leader. | ሁሉም ሰው የ Policy Council አባል ይሆናል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። ይህ በጣም አስፈላጊ ነው፣ ምክንያቱም እዚያ በመገኘት ብዙ ነገሮችን ትማራላችሁ፣ ታድጋላችሁ፣ እንዲሁም እነሱ እዚያ ያሉት እናንተን መሪዎች ለማድረግ ነው። |
| For more information about getting involved, talk with the Family Support staff at your site. | ተሳታፊ ስለመሆን ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ በጣቢያዎ የሚገኙትን የ Family Support ሥራ ባልደረቦች ያነጋገሩ። |
| Music: Memories / Sweet – Bensound.com | ሙዚቃ፥ Memories / Sweet – Bensound.com |